# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org



የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ
ጥቅምት 8 ቀን 2008 ዓ.ም የተላለፈ


ጥቅምት 2008 ዓም

## *አገርንና ወገንን የሚያስቀድም ትውልድ ማነጽ የሁሉም ኃላፊነት ነው ።*

*ከግማሽ ምዕተ- ዓመት ያላነሰ ትግል ሲያካሂድ የቆየው ትውልድ፤ በተፈጥሮ ህግ ምክንያት፤ ቀስ በቀስ ሳያውቀው በሞት እየተለየ በመሄድ ላይ ይገኛል ። ተኪውን ሳያዘጋጀ ቢያልፍ አገሪቱ ከባድ አደጋ ውስጥ ትወድቃለች። ይህ ትውልድ ሳይተካ ከሄደ ፤ ሀገሪቱ መፃዒ እድሏን ሊረከብ የሚችል ትውልድ እያጣች ትሄዳለች ማለት ነው። ስለሆነም በዚህ በኩል መፍትሔ መፈለግ ይኖርበታል ። ለዚህ መፍትሄ ካልተገኘ ደግሞ፤ ሀገርን ማዳን ቀርቶ ራስንም እንኳን ቢሆን ከአደጋ መከላከል የሚቻል አይሆንም። የታጋዮች መዳከም ወያኔ፤ ጠላቶቹን ፤ ለየብቻ እየነጣጠለ ለመምታት ምቹ ሁኔታ የፈጠረለት ሲሆን የወጣቱን ትውልድ አዕምሮ ለመስረቅ ዕድል ገጥሞታል ። የተተኪውን ትውልድ አዕምሮ ከመስረቅ የበለጠ፤ ሀገር የማጥፋት ወንጀል ደግሞ ሊኖር አይችልም ።*

*አገርን የማያስቀድም ትውልድ ይዞ ወደፊት መራመድ ቀርቶ፤ መኖር እንኳን የሚቻል አይደለም። የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ሀ ብሎ የጀመረው፤ ወያኔ እምኒልክ ግቢ ከገባ በኋላ ነው ብለው ለሚናገሩ ከንቱ ፍጡራን፤ ያሻቸውን እንዲዘላብዱ ተመችቷቸዋል ። ጋኖቹ አልቀው ምንቸቶች ጋን በሆነባት ሀገር ፤ ይህ መሆኑ ደግሞ አያስገርምም ። " ዛፍ በጠፋበት ሀገር ፤ ቁጥቋጦ ዛፍ መሆኑ " የተለመደ ነው። ዛፍ ለመሆን የተዘሩትን ቡቃያዎች፤ ደርግ ስለጨፈጨፋቸው፤ ወያኔዎቹ ባዶ ባድማ አገኙና ሰተት ብለው ገቡ ። ከዚያ በኋላ የሆነውን በመዘረዘር ጊዜ ልናጠፋ አይገባንም ። የሚያውቀው ያውቀዋልና ! ሊያውቅ የማይፈልግ ደግሞ ራሱን እያተለለ ይኖራል ። መኖር አይበለውና !*

*አንድን ሀገር፤ ህያው ሆኖ ሊኖር የሚያስችለው፤ የዜጎቹ ህልውና ተከብሮና ተረጋግጦ ሲቀጥል ነው ። የዜጎች ነፃነትና የሀገር ኅልውና ተለያይተው ሊታዩ የሚችሉ አይደሉም ። የኅልውና ትርጉሙ፤ ከነፃነት መከበር ጋር ካልታየ ፤ ትርጉም የለሽ ሆኖ ይቀራል። የሀገሪቱ ዜጎች ናቸው ተብለው የሚቆጠሩት ፤ በወቅቱ የሚኖሩት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ ያለፈውን ዜጋና የሚመጣውን ተተኪ ትውልድ ሁሉ የሚያካትት መሆን ይኖርበታል።*

*ሦስቱንም ተከታታይ ዜጎች በአንድ ሀገር የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ አስገብቶ ካልተነበበ፤ የሀገሪቱን ታሪክ በተሟላ ዕይታ ለማየት ያስቸግራል ። የልጅን፤ የአባትን፤ የአያትንና የቅድመ-አያትን ታሪካዊ ቅደም- ተከትል ትስስርና ተወራራሽነት እያገናዘቡ እያከበሩና እያስከበሩ ካላስተላለፉት ፤ ኢትዮጵያዊነት ባዶ ነበቢት ከመሆን አያልፍም ። ዛሬ የሚፈለገው ግን ይሄ ሆኗል። አኩሪ ታሪክን እያጠፉ፤ በአሳፋሪ ታሪክ መተካት፤ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ኅልውና ማጥፋት ነው። የሀገራችን ዋልታና ማገር ደብዛው እንዲጠፉ እየተደረገ ነው። ዐማርኛ ቋንቋንና ሃይማኖትን ማጥፋት፤ የሀገሪቱን ዋልታ ከማጥፋት ጋር የተየያዘ ነው።*

17 ዓመት የደርግ አምባገነን አገዛዝና የወያኔው 24+ ዓመታት ዘረኛ ሥርዓት ሲደመር፤ 41+ ዓመት መሆኑ ነው። በዚህ የዘመን ገደብ እያደገ የመጣው ትውልድ የሀገሪቱን ጠቅላላ ሕዝብ (Demography ) ፤ ቁጥር ከፍተኛውን % እንደያዘ ይገመታል ። ይህም ማለት፤ የሀገሪቱ ዜጋ በአመዛኙ በወጣት ትውልድ የተመላ ነው ማለት ያስችላል።

ይህ ትውልድ የሁለት አምባገነን እኩይ ሥርዓቶች ሰለባ ሆኗል። በሰው -በላው የደርግ ጭካኔ፤ በፍርሃት እየተሸማቀቀ ያደገውና፤ ዛሬ ደግሞ፤ በዘረኝነት የተበከለ ሥርዓት ውስጥ ገብቶ በማደግ ላይ ያለው ወጣት ዜጋ ነው ። የሁለት ሥርዓቶች ሰለባ/ተጠቂ የሆነው ትውልድ፤ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች እንዳሉበት ይገመታል ።

ደርግ፤ የፍርሃትንና የመሸማቀቅን ባኅርይ አውርሶ ሲሄድ፤ ወያኔም በበኩሉ፤ በዘርና በጎሣ መርዝ እየተበከለ እንዲያድግ እያደረገው ይገኛል። ያንዲቱ ሀገር ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆኑ እየቀረ፤ ሁሉም፤ በየጎጡና በየአካባቢው አድማስ ተወስኖ እንዲያምን እየተደረገ ነው። የቆየችዋን ጥንታዊ ሀገር እያፈራርሱ፤ በአያሌ ዘመናት ባንድ ላይ አብረው የኖሩትን ዜጎች በዘር እየከፋፈሉና እየበታተኑ፤ አዲሱን ትውልድ፤ በኢትዮጵያዊነት ስሜት ሳይሆን፤ በየዘር- ማንዘሩ፤ በየጎጥ -ጎጥጎጡ፤ በየማጀቱና ስራ- ስሩ ተከልሎ የአስተሳሰብ ድሃ ሆኖ እንዲቀር እየተደረገ ነው። ይህ የዘረኞች ዕቅድ፤ የኋላ-ኋላ እንደሚከሽፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባይጠራጠርም፤ ተከሎት የሚሄደው መርዝ ግን በቀላሉ የሚነቀል አይሆንም።

ከመሥዋዕት የተረፈው ያ አብዮታዊ ትውልድ፤ የስድሳ ስድስቱ ሕዝባዊ አመፅ ያነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች ባለመመለሳቸው ፤ በፅናት ትግሉን ቢቀጥልም፤ ተተኪውን ኢትዮጵያዊ ትውልድ የማዘጋጀት ኃላፊነት እንዳለበት በአንክሮ ይገነዘባል። ተተኪውን ትውልድ፤ ኃላፊነት እንዲሸከም ማዘጋጀት ምን ያህል ብርቱ ጥረት እንደሚጠይቅም ከልብ ያምናል። ሰፊ የትውልድ ክፍተት(Generation Gap ) እንዳለም የሚስተው አይደለም ። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ስሜት እየተሸረሸረ፤ ወጣቱ ትውልድ፤ ዘርንና ቋንቋን መሰፈርት ባደረገ ፕሮፓጋንዳ አዕምሮው እየተበረዘ መሆኑንም በሚገባ ተረድቶታል ። የዚህ ሁሉ ድምር ወጤት ሁኔታዎቹን ይበልጥ ውስብስብ ሊያደርገው እንደሚችል ጥርጥር አይኖርም።

ውስብስብነቱን በጣጥሶ ለማስወገድ ፤ የዚህ ሁሉ መርዝ ምክንያት የሆነውን ጠንቀኛውን ዘረኛ ሥርዓት መነጋግሎ መጣል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ዘረኛውን አምባገነን አገዛዝን ማስወገድ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ወጣቱን ትውልድ፤ በኢትዮጵያ ሀገራዊ ስሜት እንዲደራጅ ማድረግ ደግሞ ራሱን የቻለ ዐብይ ሥራ ነው። ይህ ዐብይ ተግባር ፤ ዐይኑን አፍጥቶ የሚጠብቀውም፤ በኅብረ- ብኄር ለተድራጁ ድርጅቶችና ስብስቦች መሆኑ ግልፅ ሁኗል።

ይህ ግንዛቤ ካለ፤ ኅብረ- ብኄር ድርጅቶች፤ ሀገርን ለማዳን ብቻ ሳይሆን፤ ተተኪውንም ትውልድ ከጥፋት ለመከላከል ሲባል እንኳ አብሮ መስራት ግዴታቸው እየሆነ መጥቷል። ተተኪውን ትውልድ፤ ለነገዋ ኢትዮጵያ ዛሬ ማዘጋጀት ካልተቻለ፤ ሀገር ማዳን የሚባል ተስፋ ሁሉ ከምኞት በላይ አያልፍም ። ባለ ራዕይ ሆኖ አስቀድሞ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ማስጠንቀቅ ካልተቻለ፤ አደጋው በሚከሰትበት ወቅት፤ የሚይዙትንና የሚጨብጡትን ማጣት ይሆናል። ዕውር-ድንብሱን የሚደረግ እንቅስቃሴ፤ የዳፍንት ጉዞ ከመሆን አያልፍም ። ጠላትንና ወዳጅን እየለዩ ካልታገሉ፤ ወዳጅ ያሉት እየከዳ፤ ጠላት ያሉት

እያበጠ ይሄዳል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ሕዝቡን ይበልጥ ተስፋ ማስቆረጡ አይቀርም ። የዚህ ሁሉ ሂደት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው፤ ወያኔ ብቻ እንደሚሆን መገንዘብ ይገባል ።

ትክክለኛ በመሆንና ጠላትን በማሸነፍ መካከል ያለውን ሚዛን ጠብቆ ካልተሄደ ፤ " የሞራል ልዕልና " መያዙ ብቻውን ውጤት አያስመዘግብም ። ውጤት ማስመዝገብ ካልተቻለ ደግሞ፤ የዘመንን ብዛት ማስቆጠሩ ብቻ የትም አላደረሰም። የሦስት ሺህ ዓመታት ትረካ፤ አሁን ካለንበት ደረጃ እልፍ ሊያደርገን አልቻለም ። በኋላችን የነበሩ አያሌ ሀገሮች እየጣሉን መሄዳቸውን ተገንዝበን ፤ ዕመርታ ለውጥ አምጥተን ማንነታችን በገቢር ካላስመሰከርን፤ የተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓቶች ሰለባ ከመሆን አንድንም ።

ሁልጊዜ ሠላማዊ ሰልፍ በማድረግ፤ ለዓለም ኅብረተስብ የአቤቱታ ደብዳቤዎች መፃፋችን ፤ የቱን ያህል እንደተናቅን፤ እንደተዋረድንና ትዝብት ላይ እንደወደቅን ማውቅ አለብን።

ሰሞኑን፤ በሊባኖስ ዋና ከተማ፤ ቤይሩት አይሮፕላን ማረፊያ ላይ በመሰደድ ላይ ያሉት በርካታ ኢትዮጵያውያት ወጣት እህቶቻችን ምን ያኅል የአደባባይ ውርደት እንደገጠማቸው ስንመለከት፤ የልብ ውጋት፤ እና የመንፈስ ስብራት እንዳስከተልብን ፤ ከእኛ በቀር ሌላ ሊረዳልን አልቻለም ። አይችልምም ።

የሥርዓት ለውጥ አስፈላጊነት ታምኖበት የተሻለ ሁኔታ ይፈጠራል በሚል ተስፋ ከፍተኛ መሥዋዕት ቢከፈልም ፤ በሀገራችን የተፈራረቁት ሦስት ሥርዓቶች፤ አፈራረቃቸው ከአንድ ጽንፍ ኋላ-ቀር ንጉሳዊ አገዛዝ ፤ ወደ ሌላኛው ፅንፈኛ የወታደር አምባገነን ጨካኝ አገዛዝና ወደ ሦስተኛው ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት ተገለባበጡ እንጅ ፤ ሕዝባችን ከመከራ ኑሮ አልተላቀቀም ። ወደ አራተኛው አምባገነን አጋዛዝ ላለመሻገር ከተፈለገ ፤ በሀገራችን ፤ የዴሞክራሲ ሥርዓት መመስረት አማራጭ አይኖረውም ። ዴሞክራሲ የሚለውን ቃል ናላ እስኪዞር ድረስ ዘወትር ቢያነበንቡት፤ ራሱ ብቻውን እስካሁን መፍትሄ አላመጣልንም ። ሕገ መንግሥት በሚባለው ሰነድ መልካም የሚባሉ ነገር ግን በሕዝብ የለት ተለት ኑሮ የማይፈተኑ አንቀፆችን ማስገባትና ነጋ ጠባ ስለነሱ ፕሮፓጋንዳ መንዛትም ፈቅ አላደረገንም ።

ዴሞክራሲ ፤ ህልው ሆኖ በገቢር እንዲገለፅ ፤ በሕዝብ ልዕልና ቁጥጥር ስር እንዲሆን ያስፈልጋል ። ዴሞክራሲ በመፈክር ደረጃ ተወስኖ እንዳይቀር ፤ ሁሉን ዜጋ የሚያሳትፍ ነፃ የፖለቲካ ምኅዳር ክፍት መሆን እንዳለበት የሚያከራክር አይሆንም ። ይህንን ለማምጣት ደግሞ ፤ የሀገሪቱን የፖለቲካ መልከዐ- ምድር፤ የነፃነት አየር እንዲነፍስበት ማድረግ ነው ። የነፃነት አየር ነፈሰ ማለት የሚቻለው ደግሞ፤ ነዋሪዎቹ፤ ያለ ስጋትና ያለምንም ተፅዕኖ ነጻ እንቅስቃሴ ማድረግ ሲችሉ ነው ። የዴሞክራሲ ባለቤቶች ሆነዋል የሚባለው፤ ከሁሉ አስቀድሞ፤ ራሳቸው ነፃ ሆነው ፤ በነፃነት የሥልጣን ልዕልናቸውን ሲያስከብሩ ብቻ ነው ። የሥልጣናችውን ልዕልና አስከብረዋል ማለት የሚቻለው ፤ በነፃነታቸው ተማምነው ፤ ከማንኛውም ኃይል ነፃ ሆነው ፤ ነፃ ምርጫ ሲያካሂዱ ብቻ ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ነፃ ምርጫ ለማካሄድ እድል አላገኘም ። ወያኔ ምርጫ አምጥቻለሁ ብሎ መቶ- በመቶ 100 % አቸነፍኩ ብሎ እራሱን አታልሎ ፤ በሕዝብ ላይ ቀልዶ ቀርቷል ። ሲያሸቃብጡለት የነበሩት ምዕራባውያን

የበላይ ጠባቂዎቹም ሳይቀሩ ስቀውበታል ። የቅርብ ወዳጁ የሆኑት አሜሪካይቱ ወይዘሮ ሶስና እንኳን በቴሌቪዥን ወሬውን ሲሰሙ፤ ሳቁ አላስችል ብሏቸው ሲንከተከቱ ታይተዋል ።

የዛሪይቱ ኢትዮጵያ፤ የገደብና የሞግዚት ዴሞክራሲ ( Guided Demoracy ) አይስፈልጋትም ። የዜጎቿ ንቃት- ኅሊና የላቀ፤ የመነጠቀና ከፍተኛ ደርጃ የደረሰ ሆኗል ። ሕዝቡ፤ ከሦስት ፀረ- ዴሞክራሲ መሪር አገዛዝ በቂ ተመክሮን አግኝቷል ። ለዴሞክራሲ ፤ ለፍትኅ-ርትዕ ፤ ለሕዝብ እኩልነትና ለሀገር ሉዓላዊነት ሲባል የተከፈለውን መሥዋዕትነትና የወድቁለትን ሰማዕታት ልጆቹንም በከብር ያስታውሳል። " ዴሞክራሲ ያለ ገደብ ! " ሲሉ የተዋደቁትን አርበኞች ዋጋ የሚከፍለውም ፤ የነፃነት ሉዓላዊነቱን በተጨባጭ ሲያረጋግጥ ነው ። ያ ደግሞ ፤ የሚገኘው በአማላጅና በልመና ሳይሆን፤ በትግል መሆኑን፤ ከሠማዕታት ልጆቹ ትምህርት ቀስሟል ። ጊዜውን እየጨረሰ ለሚሄድ አልፎ- ሂያጂ አምባገነን አይምበረከክም ። በትግሉ ያንበረክከዋል እንጅ !

ለአለፉት አምሳ ዓመታት ፤ በሦስት የዘመን ክልል የነበረውን/ ያለውን ትወልድ ኃይል አስተበብሮ፤ ለሀገር ግንባታ ለማሰለፍ የሚችል መንግሥት አልነበርም ። አሁንም የለም ። ያ መሆኑ ቀርቶ እንዲያውም ትውልድን በመደብ ፤ በዘርና ቋንቋ እየከፋፈሉ ማፋጀት ነበር ። ነውም ። ያ ትልቅ ጉዳትና ዕልቂት አስክትሎ ነበር። አሁንም ሁኔታው እንደቀጠለ ይገኛል ። ይህ ሁኔታ ሊቀጥል አይገባውም ። ሂደቱ አንድ ቦታ ሊሰበር ይገባዋል። ኢትዮጵያ የቅርስና -ውርስ ሀገር ነች ከተባለ ፤ የቅርሱን ዓይነተኛ ቦታ ሊይዙ የሚገባቸው፤ ዜጎቿ ናቸው። ይህንን አመለካከት የሚረዳ ዜጋ ሁሉ፤ ትውልዱን በሙሉ የማክበርና የመንከባከብ ኃላፊነት እንዲሸከም ይጠበቅበታል።

ኃላፊነቱን በይበልጥ ለመሸከም የሚጠበቅባቸው ደግሞ ፤ በኅብረ ብኄር ተዋቅረው የተደራጁ ናቸው ። ምክንያቱም፤ ኢትዮጵያን የሚመለከቷት እንደ ኪራይ ቤት ሳይሆን ፤ እንደ ዘለዓለማዊ ሀገራቸው አድርገው ስለሚያምኑባት ነው። " ለእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ! " ከሚሉት ክፍሎች ጋር ፤ በዕምነትም ይሆን በአመለካከት አይገናኙም ። በዚህ ምክንያት ፤ እስከ ዛሬ ድረስ በኅብረት ለመስራት ሳይቻል ቀርቷል ። ይህ ልዩነት ካልተወገደ ፤ ወይም ደግሞ ካልጠበበ ፤ አብሮ የመስራቱ እድል እንደጠበበ ይቆያል ። ዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ ህያው ሆና መቀጠል አለባት የሚለው የአንድነት ኃይል ጠንክሮ ከወጣ፤ ( መውጣትም አለበት ) ልዩነቱ ሊጠብ ይችላል ብለው የሚያምኑ ቁጥራቸው በእጅጉ በርካታ ነው። " ኢትዮጵያ መኖር አለባት " የሚለው ኃይል፤ የማታ ማታ አቸናፊ ሆኖ እንደሚወጣ ማንም ሊጠራጠር አይችልም። የጊዜ ጉዳይ ነው ! ጊዜው ሳይመሽ ሁሉም ሰልፉን አሁኑኑ ማሳመር አለበት !

የወጣቱን ትውልድ ኃይል ለማሰባሰብ ፤ መጀመሪያ ፤ የዚህን ትውልድ፤ አመለካከቱንና አስተሳሰቡን ፤ ቋንቋውንና አነጋገሩን ፤ ፍላጎቱንና መስተጋብሩን፤ ራዕዩንና ምኞቱን ሁሉ በጥልቅ ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል ። በአርባና አምሳ ዓመታት መካከል ያለው የትውልድ ልዩነት፤ ስፋቱ ቀላል አይሆንም። የስድሳ ስድስቱን ( 1966 )፤ የካቲት ነባራዊ ሁኔታዎች አሁን ስለሌሉ፤ ለሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን የሚስማማውን ዝግጅት አድርጎ መቅረብ ወስኝ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን በአርባና አምሳ ዓመታት ውስጥ ከሃያኛ ክፍለ-ዘመን ወደ ሃያ አንደኛው ክፍለ -ዘመን መሸጋገሯን ማጤን ይገባል ። በዚያ

በታገለው) ትውልድና በዚህ (በወጣቱ ) ትውልድ ሊኖር የሚችለውን ክፍተትና ልዩነት እያጠበቡ በአንድ ብሄራዊ ዓላማ ለማሰለፍ የሚቻለው፤ የተራቀቀ ( Sophisticated ) ዘዴንና ብልሃትን የያዘ ሀገራዊ ፖሊሲን ነድፎ በተግባር ለመተርጎም ሲቻል ነው። የወያኔ ረጋ-ሰራሽ (Artificial ) ፖሊሲ ከፕሮፓጋንዳ ፍጆታና የውጭ ምፅዋዕት ከማግኘት የበለጠ ጥቅም የለውም። ያም ቢሆን ከጊዜያዊነት አያልፍም ።

የነገዋን ኢትዮጵያ የሚያስተዳድር መንግሥት ሆነ ሥርዓት፤ ከሁሉ አስቀድሞ የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅምና ፤ የሕዝቧን ደህንነትና ፍላጎት የሚያስጠብቅ እስካለሆነ ድረስ ፤ አሮጊውን በአዲሱ መተካቱ ትርጉም የለሽ ሆኖ ይቀራል ።

ዛሬ፤ በዘረኞች ፖሊሲ የምትገዛዋ ሀገራችን የሚከተሉት ገፅታዎች ይታዩባታል :-------

1. ደሙን አፍስሦ ጨርሶ፤ እምባውን እየተመገበ የሚኖር ሰባት (7) ሚሊዮን በላይ ረሀብተኛ ሕዝብ አለባት ።

2. በበርካታ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝቧ ሀገሪቷን እየለቀቀ በመሰደድ ላይ ይገኛል ። ከዚህ ቁጥር ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ወጣቱ ትውልድ ሆኗል ። የስደቱም ዓይነተኛ ምክንያቶች ፤ የሰብዓዊ መብቶች አለመከበር፤ በሠላም ሰርቶ መኖር አለመቻል ዋናዎቹ ናቸው ።

3. በዕምነታቸው፤ በፖለቲካ አመለካከታቸውና፤ በብሄር ልዩነታቸው ብቻ ወህኒ ወርደው የሚሰቃዩትን ዜጎች ቁጥር በትክክል ማወቅ የማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል ። የጅምላ ግድያና ጭፍጨፋ የዕለት ተዕለት የሥርዓቱ ተግባርና ባኅርይ ሆኗል ።

4. የወያኔ ባለስልጣኖች፤ በሙስና፤ በዝርፊያ የሀገሪቱን ሀብት ወደ ውጭ አሸሺተዋል። አሁንም የሚያሸሹበት ሰፊ ዕድል አላቸው።

5. የሀገሪቱ ብሄራዊ ሀብት ፤ ለውጭ ዜጎች መጠቀሚያ እየዋለ ፤ የሀገሪቱ ዜጎች የበይ- ተመልካቾች ሆነው ቀርተዋል ።

6. ወጣቱ ትውልድ ፤ ሆን ተብሎ፤ በአልባሌና አደገኛ ባኅል እየተበከለ እንዲያድግ እየተደረገ ነው ። በአድንዛዥ ዕፅ፤ አዕምሮው እንዲበከል ሆኗል ።

7. የሀገሪቱ የውጭ ፖሊሲ የተነደፈው ፤ የምዕራቡን ጥቅም ለማስጠበቅ ነው ። ኢትዮጵያም ፤ በአዲሱ የእጅ -አዙር ቅኝ አገዛዝ ስር ወድቃለች ። ሀገር-ወዳድ መንግሥት እስካልተቋቋመ ድረስም ፤ የሀገራችን ሉዓላዊነትና ብሄራዊ ክብሯ እንደተደፈረ ይቆያል ።

ዝርዝሩ ብዙ ነው። ታዲያ፤ ሁኔታውን ለመለወጥ ምን መደረገ አለበት? ለሚለው ጥያቄ ፤ ሁሉም የበኩሉን መልስ እንዲያዘጋጅ ጥሪያችንን ማስተላለፋችንን እንቀጥላለን ። ፈቀደኛና ዝግጁ ሆኖ ከቀረበ ከአንድነት ኃይል ጋርም

እንተባበራለን ። ሀገራችንን ለአዲስ ዓይነት ቅርጫ ከሚያዘጋጁት ጋር ግን ግንኙነት አይኖረንም ። ወጣቱን ትውልድ ለሀገራዊ ትግል እንዲሰለፍም ጥረታችንን እንቀጥልበታለን ። ሀገርን የማዳኑ ተግባር ከፍተኛ መሥዋዕትን የሚጠይቅ እንደሆነ በአንክሮ ስለምንገነዘብ ፤ እስከመጨረሻው እስትንፋስ ድረስ ከመቀጠል በቀር ሌላ አማራጭ አይኖረንም። በዚህ ቁርጠኝነት ከተዘጋጁት ጋር ለመተበባር ጥሪ እናስተላልፋለን !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !